# በፀረ ሙስና ትግሉ  የታክስና ንግድ ነክ ጉዳዮችም ቢፈተሹ

ዮናስ 05/21/13

በአለም ላይ ያሉ ሃገራት ለልማት የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ከሚያገኙባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው የታክስ ገቢ ሲሆን፣ ከብሄራዊ ገቢው ውስጥ የሚኖረው ድርሻ እንደየአገሮቹ የልማት ፖሊሲ፣ የዕድገት ፍጥነትና የልማት ደረጃ እንዲሁም የማስፈፀም አቅም የተለያየ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ በሌላ በኩል ታክስ የአገር ልማትን አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያገለግል የፖሊሲ መሳሪያም እንደሆነ የዘርፉ ልሂቃን አስምረውበታል፡፡ እነዚህ ተመራማሪዎች የልማት ፖሊሲን ማሣካትና መክፈት /optimizing Economic growth/ እና ፍታሃዊነትን በሁሉም የልማት  ዘርፎች ማስፈን /Ensuting Equity/ የታክስ ሚና እንደሆነ ጨምረው እና አበክረው ይገልጻሉ፡፡ ደረጃው የሚለያይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በየትኛውም ሃገር መንግስት ዓላማውን ለማሳካት እንዲቻል በማሰብ ህጉን ለማስከበርና አስተዳደሩን ፍትሃዊ ለማድረግ በሚደረገው ጥረትና ግብር ከፋዩ ግብርን ላለመክፈል ባለው ትንቅንቅ መካከል ችግሮች መከሰታቸው አይቀሬ ነው፡፡

ይህንን በታክስ አስተዳደሩና በግብር ከፋዩ መካከል ባለ ህግ የማስከበርና ያለአግባብ የመበልፀግ ተቃራኒ ፍላጎቶች መካከል የሚፈጠረውን ችግር ሃገራት በተለያየና አግባብነት ባለው የፖሊሲ ማዕቀፎች ለማስታረቅ ቢሞክሩም አብዛኞቹ አልተሳካላቸውም፡፡ በተለይም እንደኛ ባሉና በማደግ ላይ በሚገኙ ሃገሮች ታክስ የልማቱ መሰረትና መዘውር በሆነበት ሂደት ውስጥ ከላይ በተጠቀሱት ጎራዎች መካከል የሚፈጠሩ ችግሮችን በጥቀመኝ ልጥቀምህና በእከክልኝ ልከክልህ ህገወጥ አግባብ ለማስታረቅ መሞከርና ከህዝቡ ጥቅም ይልቅ ሃላፊነት የተሰጠው አካልና ግለሰቡ ከጥቂት ደላሎች ጋር ሆነው በሚገርም ሁኔታና ከሞራልም በላይ በሆነ አሳፋሪ ሁኔታ ተምዘግዝገው ወደላይ ሲወጡ ይስተዋላል፡፡

ይህን በተመለከተ በሁለቱ ወገኖች መካከል በተፈጠረው የጥቅም ግንኙነት የተፈጠረውን ጉድለት ለማካካስ ሲባል ትንንሽ ነጋዴዎችን እና መላውን ህብረተሰብ መስዋዕት ማድረግ የተለመደ ነው ሲሉ አንዳንዶች በተደጋጋሚ ቢያወሱም የሰማቸው ያልነበረ ሲሆን ምንም

እንኳ የረፈደም ቢሆን አሁን ግን ችግሩን ከእናቱ ጀምሮ ለማጥራትና የእከክልኝ ልከክልህ የድርና ማግ ትስስራቸውን የመበጣጠስ እርምጃ የተጀመረ ይመስላል።

በዚህ መሰረት እና ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት በተለይም የግል ጥቅምን በአንድ በኩል፤ እቅድ ማሳካትን በሌላ በኩል ይዘው አንዱን በአንዱ ለመድፈን በሚያደርጉት መወራጨት ደሃውና ልማታዊው ነጋዴ ያለአግባብ እየተመታ ያለበት ሁኔታ ከመኖሩ ጋር በተያያዙና የተጀመረውን የፀረ ሙስና ትግል ለማኮላሸት የሚወረወሩ ቅጣምባራቸው የጠፋ ምናልባትም የተዋናዮቹ ግብረ አበሮች አስተያየት እየሰፋ በመምጣቱ በዚህ ጽሑፍ የታክስ አስተዳደሩ አሁንም እንዲፈተሽና ትግሉም በሌሎቹም ዘርፎች ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው መሆኑን የሚያሳስቡ አንዳንድ ነጥቦችን አነሳለሁ፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶችና ችግሮች መነሻነት የታክስ አሰባሰቡ ደካማና ታክስ ሰብሳቢውም ጠንካራ የማስፈፀም አቅምና ስልጣን የሌለው እንደነበር ይታወቃል፤ በዚህም ሳቢያ ሊሰበሰብ የሚገባው የመንግሥት ገቢ እንዳይሰበሰብና በርካታ የታክስ ማጭበርበርና ምዝበራ የሰፈነበት የግብር አስተዳደር ሥርዓት ሰፍኖ ቆይቷል።

እነዚህ የታክስ ፖሊሲና የታክስ አስተዳደር ድክመቶች  መፈታት ያለባቸው ችግሮች መሆናቸው ግንዛቤ አግኝቶ የታክስ ስርዓት ፍትሃዊ ዘመናዊና ለማስተዳደር ቀላል ይሆን ዘንድ የግብር ህጉን በማደስና የታክስ አስተዳደሩን በማሻሻል ላይ ማተኮር ተገቢ እንደሆነ ይታመናል። መንግሥት ልማታዊ የታክስ አስተዳደር መገንባትንና ለዚህም ለልማታዊ ባለሃብቱ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲሁም የኪራይ ሰብሳቢነትን መንገድ ለመዝጋትና ገቢን በወቅቱና በብቃት ለመሰብሰብ ግብ ያደረገ የታክስ አስተዳደር ማሻሻያ ስርዓት በቅርቡ ተግባራዊ ማድረጉም ይታወቃል። ከእነዚህ ማሻሻያዎች ውስጥም በመረጃ ስርዓት ዝርጋታ፣ የግብር ከፋይ ግንዛቤ በማሳደግ፣ ከቀድሞው ለወጥ ያለ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋትና የሰው ሃይልን በማብቃት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥቶም ለመንቀሳቀስ ሞክሯል። ይህ ሁሉ ተደርጎም ግን የሚፈለገውን ያህል ፈጣን ለውጥ ማምጣት እንዳልተቻለ ጠቅላይ ሚንስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ ባለፈው ሰሞን የበጀት ዓመቱን የ8 ወራት ሪፖርት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረቡበትና ወቅት ተገልጿል። የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አፈፃፀም ከታቀደው እጅግ  በጣም ያሽቆለቆለ እንደሆነም ተረጋግጧል።

ይህም ብቻ ሳይሆን የታክስ አስተዳደሮቹ ገና በደንብ ሊፈተሹ እንደሚገባቸው በተናገሩበትና በተቋሙ ስፋት ያለውና ስር የሰደደ የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር እንዳለ ባመለከቱና ጥቆማ በሰጡ ማግስት የባለስልጣኑ ዋናና ምክትል ዋና ዳይሬክተሩን ጨምሮ ሌሎች የባለሥልጣኑና ቅርንጫፍ ጽቤቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ውለዋል፡፡

ብዙዎቹ (ይህም ከባለሥለጣኑ ግንዛቤ የመፍጠር አቅም ችግር ወይም ዳተኝነት ጋር የተያያዘ ነው) የመንግሥት ቀረጥና ታክስ የሚባለው የመንግሥትን የልማት እቅዶች ለማስፈፀም የሚያስችል ገንዘብ ለመሰብሰብ ብቻ ቢመስላቸውም የዘርፉ ልሂቃን የመንግሥትን የልማት እቅዶች ከማስፈፀም ጋር የተያያዘው ጉዳይ ዋና ቢሆንም ከዚሁ ያልተናነሰና ይልቁንም ተያያዥ የሆነ ከፍተኛ ጥቅም ያለው መሆኑን ያወሳሉ፡፡ በተለይ በእኛ ሃገር ተጨባጭ ሁኔታ ልማትን ማፋጠንና ኢንቨስትመንትንና ልማታዊ ባለሃብቱን ማበረታታት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ የታክስ ፋይዳዎች ናቸው፡፡ ኢንቨስተሩና ልማታዊ ባለሃብቱን በመደገፍ ረገድ የግብር አሰባሰብ ስርዓቱ በመሰረቱ ከተቀየረ በውስጡ የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህ ያካተተ ቀላልና ቀልጣፋ አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ ስለሚገኝ የኪራይ ሰብሳቢዎች ጫካ ይመነጠራል፡፡ ስርዓቱ ራሱን በራሱ ለልማታዊ ባለሃብቱና ኢንቨስተሩ የተመቻቸ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ የጥገኞች መዳከሚያ መሳሪያ ይሆናል ይላሉ ልሂቃኑ፡፡

በዚህ መሰረት የታክስ አስተዳደር ማሻሻያ ስርዓት ተገንብቶ በተግባር ሂደት ውስጥ ይገኛል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮም ቢሆን ግብር ከፋዮች ከግብር አስከፋዩ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ብዙዎች በገገርና ሎሌ ወይም በአልቃሽና አስለቃሽ ይመስሉት እንደነበርም ይታወቃል። አንዳንዶቹ ባለሃብቶች ደግሞ ተቋሙን ቤታቸው እስኪመስል ድረስ ሲያተራምሱትና ሃላፊነት የተሰጣቸውን አካላትም በጥቅም አስረው እንዳሻቸው እየነዱቸው እንደሆነ የሚሰጠው አስተያየት በርግጥም ትክክል እንደሆነ፣ በተለይም የግብር ከፋይ ተመዝጋቢው ቁጥርና የንግድ እንቅስቃሴያችን እንዲህ በሰፋበትና የኢንቨስትመንት አማራጩም በተመሳሳይ ያደገበት ሁኔታ ያለ ስለመሆኑ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የገቢ አፈፃፀም አመላክቷል፡፡ ነገር ግን ሙስናው በእነዚህ ስልጣናቸውን ያለአግባብ በተጠቀሙና በህዝብ አደራ ላይ በወሰለቱት ጥቂት የጉምሩክ ባለሥልጣናትና ጥቂት “ባለሃብቶች” ብቻ ተከናወነ ማለት የዋህነት ነው፡፡ ሥለሆነም ብርበራውንና

እርምጃውን መቀጠሉ እንዲያም ሲል እስከታች ድረስ ወረድ ብሎ መፈተሽ ተገቢ ይሆናል።

ከቀረጥና ታክስ ማጭበርጨር በተጨማሪ ሌላ የገቢና የወጪ ንግዳችንን እየጎዳ ያለው የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን በብቃት ካለመከላከልና የባለሥልጣኑ የሥራ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች ከህገወጦች ጋር የሚያደረጉት ያልተገባ ድርድር እንደሆነም ጠቅላይ ሚኒሥትሩ አመልክተው እራሳቸው በግላቸው እንደሚከታተሉት ቃል በመግባት የማስረጃ ያለህ ማለታቸውም የማይዘነጋና ፍልሚያው ከገዛ ጥቅማችን ጋር የተያያዘ በመሆኑ ለጥሪያቸው አቤት ልንል የሚገባን መሆኑ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

በኢህአዴግ 9ኛ ጉባኤ ላይ እና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት ላይ በተመሳሳይ እንደተወሳው ይህን ችግር ማስወገድ ያልተቻለው ችግሩ በኪራይ ሰበሳቢ ኮንትሮባንዲስቶችና አጭበርባሪዎች ብቻ የሚፈፀም ሳይሆን በየደረጃው በተሰገሰጉ ሙሰኛ የመንግሥት አስፈፃሚ አካላትና በየደረጃው ባሉ ሰራተኞችና አቀባባዮች የሚደገፍ በመሆኑ በዚያ መልክ መንግሥት ለማጥራት የሚያደርገውን ትንቅንቅ አብዛኛውን ግብር ከፋይ እና ህዝቡን ሳያሳትፍ ሲተገብር በመቆየቱ ነው ትግሉ ያልተሳካው ተብሏል፡፡ ስለሆነም ልማታዊውን ነጋዴና ባለሃብት ለማጠናከርና ህገ ወጡን ለማዳከም የሚያስችል ስርዓት የመገንባቱ ጉዳይ ገና ብዙ ሥራ የሚቀረው መሆኑን በመገንዘብ መንግሥት ተከታታይ የሆነ የፖለቲካ ኢኮኖሚውን የመቀየር ትግል ማድረግ እንዳለበትና በህዝቡ ንቅናቄ ላይ የተመሰረተ አስፈፃሚውን የማጥራቱን ሥራ ማከናወን እንዳለበትና ከዚህ ንቅናቄ ውጪም ትግሉ የማይሳካ እንዲሆነ ማመን አለበት፡፡ ሥራው ደግሞ የአንድ ሰሞን የዘመቻ ሥራ ሳይሆን ተገቢው ሥርዓትና ቅንጅታዊ አሰራር ተበጅቶለት ቀጣይነት ባለው መልኩ ሊሰራ ይገባዋል።

ወደ ግብር ሥርዓቱ ያልወጡት የአየር ባየር ነጋዴዎች ደረጃ በደረጃ በህጉም በተከታታይ ከሚወሰዱ እና ሰሞኑን ከተወሰዱቱ እርምጃዎች እንዲማሩ በማድረግ ወደግብር ሥርዓቱ እንዲገቡ ማድረግ፣ በቀረጥና ታክስ ማጭበርበር ሥራ ላይ የተሰማሩትን ድርጊቱ እንደሚያስቀጣቸው የማስገንዘብ፣ በህግና አፈፃፀም ቀዳዳዎችን በመዝጋት ይበልጥ ወደልማታዊና ህጋዊ አቅጣጫ የሚገቡበትን በር ዳግም በማስፋትና በድርጊታቸው የሚገፉበትን እንዲከስሙ የማያዳግምና ተከታታይነት ያለው እርምጃ መውሰድ ለነገ የማይባል የመንግሥት ተግባር መሆን አለበት፡፡

ህዝቡም ይህንኑ እየጠየቀ ስለመሆኑ የሰሞኑ የካፌዎች አጀንዳ ዋቢያችን ነው፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ጠቅላይ ሚንስትሩም እንዳሉት አብዛኛውን ግብር ከፋይ በማሳተፍ በማሳመን፣ ሰፊውን የልማቱ ተጠቃሚና ባለቤት የሆነውን ህዝብ ግንዛቤና ተሳትፎ በማጎልበት ሙስናን መፋለም የሚቻል በመሆኑ ህዝቡም ከካፌ አጀንዳነት በዘለለ ተሳትፎውን አንድ እርምጃ ወደፊት ማስቀጠል ይጠበቅበታል፡፡ መንግሥት በበኩሉ በጥቂት ግብር ሰዋሪዎች ብዙሃኑ የሚደናበሩበትን አቅጣጫ በመተው አብሮ ሊሰለፍ የሚገባው ግብር ከፋይ የማይደናገርበትንና የማይደናበርበትን መንገድ ሊከተል ይገባል፡፡

በሌሎች ዘርፎች በመሬት አስተዳደርና መሰል ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ላይ እርምጃው ማስቀጠል እንደተጠበቀ ሆኖ በገቢዎችና ጉምሩክ ላይ አሁን የተወሰደው እርምጃ እንዲቀጥልና የመንግሥት ቁርጠኝነት በተግባር እንዲገለፅና ከነዚህም ጋር ሌሎች አጭበርባሪ የመንግሥት ሙሰኞች፣ነጋዴዎችና ደላሎች ላይ የተጠናከረ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል።

ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አላማዎች አንዱ ግብርን በፍቃደኝነት የመክፈል ባህል እንዲዳብር ማድረግ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ይህን መሰረታዊ አላማ ለማሳካት እና እርምጃው እስከታችኛው የገቢዎችና ጉምሩክ መዋቅሮች እንዲወርድ ህብረተሰቡ ስለግብርና ታክስ እንዲያውቅ በተጨባጭ እየታየ ካለው ልማት ጋር አስተሳስሮ እንዲገነዘብ ማድረግ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት ለነገ የማይባልና ከመንግሥት የሚጠበቅ ቁልፍ ተግባር ሊሆን ይገባዋል፡፡ ለምን ቢባል የራሱን ግብር በወቅቱና በልኩ መክፈል ብቻ ሳይሆን ሌላውም እንዲከፍል እና እንዲታገል አጭበርብሮ የተገኘውንም ለማጋለጥ እንዲተጋ ያበቃልና፡፡ ግብር ከፋዩም በሥራ ላይ የዋሉትን የግብርና የታክስ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች እንዲያውቅ በማድረግ በትክክል መብትና ግዴታውን እንዲያውቅና ከማድረጉም በላይ ወደጥፋት በል በል የሚሉት እጆቹን ሰብሰብ ለማድረግ ያስችለዋል፡፡

በገቢዎችና ጉምሩክ ሥራዎች ውስጥ በቀረጥና ታክስ ማጭበርበርና የተቋሙን አላማ ከማሰናከል አንፃር ትልቅ ድርሻ ያላቸው የስጋት አካባቢዎች (Sensitive areas) መለየታቸው የትግሉ ማቀጣጠያና አንድ እርምጃ የሚያስኬድ የፀረ ሙስና ትግሉ መደላድል ነው፡፡ የኮንትሮባንድ ንግድ፣ የንግድ ገቢ ወይም ትርፍ ማጭበርበር፣ በመንግሥት የተሰጡ የቀረጥ ነፃ መብት ማጭበርበር፣ የዋጋና ታሪፍ ማጭበርበር፣የግብር

መወሰኛና የተደራጀ የቀረጥና ታክስ ማጭበርበርና ያልተፈቀዱ ወይም ከደረጃ በታች የሆኑ ምርቶችን በማስገባት መሸጥ፣ የዘርፉ የሥጋት አካባቢዎች መሆናቸው አስቀድሞ መለየቱ በርግጥም በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር የዋሉ የባለሥለጣኑ ከፍተኛ የሥራ ሃላፊዎችና “ባለሃብቶች” የተጠረጠሩበት የክስ መዝገብ አረጋግጦልናል፡፡

ከሰሞኑ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከፍተኛ የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች እንዲሁም ጥቂት ከፍተኛ ነጋዴዎች በተጠረጠሩበት ወንጀል መያዝ ሌላም የሚያስገነዝበን ነገር አለው፡፡ ይኸውም በጉሙሩክና በታክስ የሚፈፀሙ ማጭበርበሮች በታለመ፣ በታቀደና በተደራጀ መንገድ የሚፈፀሙበት ዕድል እንዳለና ከጉምሩክ አንፃር አንዳንድ ላኪዎች፣ አስመጪዎች ትራንዚተሮችና የጉምሩክ ሰራተኞች በከፊል የሚሳተፉበት ሁኔታ እንዳለ እና ህብረተሰቡም የዘርፉን የማጭበረበር ሰንሰለቶች የትኞቹ እንደሆኑና እስከየት ድረስ ሊረዝሙ እንደሚችሉ በመገንዘብ ተሳትፎውን በየት በኩልና በየትኛው አቅጣጫ ላይ ማድረግ እንዳለበት ግንዛቤ ፈጥሯል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በመሬትና መሰል የኪራይ ሰብሳቢነት መነኻሪያ የሆኑ ማዘጋጃ ቤታዊ ጉዳዮች ቀጣይ የመንግሥት የትኩረት አቅጣጫ መሆናቸው እንደተጠበቁ ሆነው በገቢዎችና ጉምሩክ እንዲሁም የንግዱ ዘርፍ ላይ የሚቀሩና በአፋጣኝ ሊታዩ የሚገባቸው ህዝብን ቀፍድድው የያዙ የሙስና መነኻሪያ ቦታዎችም መኖራቸውን መንግሥት ያውቃቸዋልና ፊቱን ወደእነርሱም ያዞር ዘንድ ህብረተሰቡ ይጠብቃል።

ይኸውም ከታክስ ማጭበርበር አንዳንድ አስመጪዎች እና አምራቾች ከአስመጪነት(አምራችነት) እስከ አከፋፋይነት ጅምላ ሻጭነት ብሎም ቸርቻሪነት በዝምድና የተመሰረተ ሰንሰለት ዘርግተው የታወቁ ካምፓኒዎቻቸው ኪሳራ እንዲያሳውቁ በማድረግ ትርፉን በተበታተኑ ቸርቻሪዎቻቸው አማካኝነት እየሰበሰቡ የመንግስትን ቀረጥና ታክስ የሚያጭበረብሩ እንደሆነ በግልጽ ይታወቃልና እነዚህም እንዲታዩ ህዝብ እየጠየቀ ነው፡፡ የህዝብ ትብብር ያሻኛል የሚለው መንግስትም የህዝቡን ጥያቄና ጥቆማ በመገንዘብ ምናልባትም የጀመረውን ጥናትና መረጃ የማሰበሰብ ሥራ በቶሎ በማጠናቀቅ ወደ እርምጃ ቢገባ ትግሉን የበለጠ ለማፋፋምና በልማታችን ቀጣይነትም ላይ እርግጠኛ እንድንሆን ያስችለናል፡፡